# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

22




መጋቢት ፲፰—፲፱፻፸፬ ዓ.ም.

### ርእሰ አንቀጽ

# አጥቂነቱ እንዲሠምር

የኢትዮጵያ አብዮት ከፊቱ የሚደቀኑትን እንቅፋቶች እየጨፈላለቀ በከፍተኛ ፍጥነት ወደፊት በመገሥገሥ ላይ ይገኛል ። ትናንት አብዮቱ ዱብ ዕዳ የሆነበትና ግራ የተጋባው አድኃሪም ሆነ ባላሰበውና ባልተዘጋጀበት ወቅት እንደ ደራሽ ውሃ የተጥለቀለቀው ተራማጅ ዛሬ በየፊናቸው ተደራጅተው ለሞት ሽረት የመጨረሻ ፍልሚያ በሁለቱ ተፃራሪ ግንባሮች ተሰልፈው በመዋጋት ላይ ናቸው ። እርጌ መሣሪያውን አንግቦ የመሬት ለአራሹን አዋጅ ለማደናቀፍ ጫካ በመግባቱ «አድኃሪ ቢሸፍት ከሶደሬ አያልፍም» እየተባለ የተዘበተበት ሁሉ በተናጠል ከመፍጨርጨር ደረጃ አልፎ ከአገር ውስጥ አጋሮቹ ከጐረቤት አገር አድኃሪ መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር እርኩስ የትግል ኅብረት መሥርቶ የተቀነባበረ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊው ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጐኑ በተሠለፉት ሀቀኛ ተራማጆች መሥዋዕትነት በአለፉት ሁለት ዓመታት በአካሄደው መራራ ትግል በአብዮቱ የተቀዳጃቸውን ድሎች ላለማስነጠቅና አዳዲስ ድሎችንም ለመቀዳጀት በገበሬ ማኅበሮች፤ በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲሁም በልዩ ልዩ የሙያ ማኅበራት እየተደራጀ ለበለጠ ንቃትና ለጠንከረ አብዮታዊ ድርጅት በመታገል ላይ ይገኛል ።

ጥር ፳፮ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ውስጥ በሚገኙት ሐቀኛ ተራማጆች ቆራጥ እርምጃ ለአድኃሪያን አመቺ ሁኔታ በመፍጠር አብዮታውያንን ሲያስመታና የቅልበሳ ሴራ ሲጠነስስ የቆየው የውስጥ አርበኞች ቡድን እናቱን ከተመቻ ወዲህ አብዮታችን ወድቆበት ከነበረው የተከላካይነት ደረጃ ወደ አጥቂነት በግብር ተሸጋግሯል ። ትናንት ከአድኃሪያን ጥቃት ራሱን ማዳኛ መከላከያ መንገድ አጥቶ ሲራወጥ የነበረው ጭቁን አርሶ አደር ፤ ወዝአደር፤ ታጋይ ወጣት ተማሪ፤ ምሁርና አብዮታዊ መለዮ ለባሽ ክንዱን አስተባብሮና ለጊዜው በአገኘው መሳሪያ ታጥቆ በታሪካዊ ጠላቶቹ ላይ የጥቃት ዘመቻ ከፍቷል ። ትናንት በአብዮታውያን ሰፈር ሰፍኖ የነበረው ሽብር ወደ አድኃሪያን ሰፈር ተጋብቷል ። ሰፊው ሕዝብ ቀንደኛ ጠላቶቹን በእየስፍራው እያጋለጠ በመምታት ላይ ነው ።

የኢትዮጵያ ወዝአደር በዚህ በተፋፋመ ሕዝባዊ አመጽ ውስጥ በፈጸማቸው ድርጊቶች የአብዮቱ ሰፈር ግንባር ቀደም ብቁ መሪ መሆኑን በሚገባ አስመክሯል በየፋብሪካው ውስጥ የተሰገሰጉትን የአድኃሪያን ቅጥረኞችና አስመሳይ ተራማጆች አጋልጦ በመምታት ብቻ ሳይወሰን አብዮታዊው አመጽ ከድርጅት ድርጅት ተዛምቶ በአካባቢው የሚገኙትን ታጋይ አርሶ አደሮችና ታጋይ ጭቁን ወጣቶች እንዲያቅፍ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው ። ለዚህም በቅርቡ የአቃቂ ከተማ ወዝአደሮች የከተማዩቱን ሀቀኛ ተራማጅ ወጣቶችና የአካባቢዋን ጭቁን አርሶ አደሮች በማስተባበር በአድኃሪያን ላይ ቆራጥ እርምጃ ለመውሰድ ያላቸውን ፍላጎት በኅብረት ለመግለጽ



እንዲችሉ ማድረጋቸው ቋሚ ምስክር ነው ። የአቃቂና የአዲስ አበባ ወዝአደሮች የአድኃሪ ወጣቶች መፈንጫ የሆኑትን ትምህርት ቤቶች ለማጽዳት ቆርጠው በመነሣታቸው ተራማጅ ወጣቶችን አስተባብረው ከጥቂት ቀናት በፊት ሲያሳድዷቸውና ፋሽስታዊ ግፍ ሲፈጽሙባቸው በነበሩት ግልገል ፋሽስቶች ላይ ክንዳቸውን እንዲያነሡ በማድረግ በኩል የፈጸሙት ተግባር ያ ወጣቱን በወጣትነቱ ብቻ እንደ አብዮታዊ አድርጎ ከማየትም አልፎ እንደ አብዮቱ ግንባር ቀደም መሪ አድርጎ የሚያቀርበው ግብዝ አስተያየት ዳግመኛ ተመልሶ ላይመጣ ጨርሶ ማከተሙንና የአብዮቱ ሀቀኛ ባለቤትና ግንባር ቀደም መሪ ታሪካዊ ሚናውን መጫወት መጀመሩን ያበስራል ። ታጋይ ወጣቶችም እንደአቃቂና ተግባረ እድ ተማሪዎች ይህን ሀቅ ተገንዝበው ከጐናቸው ተሰልፎ በአጥንቱና በደሙ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ ቆርጦ ከተነሣው ወዝአደር ጋር የተቀራረበ የትግል አንድነት መመሥረትና ትግሉን በበለጠ ማፋፋም ይኖርባቸዋል ።

ሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ በተለይም ወዝአደሩ ከከፍተኛው የትግል ደረጃ ማለትም ከትጥቅ ትግል ውስጥ ገብቷል ። ሆኖም ትግሉን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስተባብርለትና ወደ ድል ሊመራው የሚችል የኮሙኒስት ፓርቲ ባለመቋቋሙ ከፍተኛ ድክመት ይታይበታል ። ከዚህም የተነሣ ወዝአደሩ የሚጠበቅበትን ያህል አስተዋጽኦ ለማድረግ አይችልም ። ይህን ድክመት ተገንዝቦ በአብዮት ሂደት መፋጠን የተነሣ ከዕለት ዕለት ከጠላት ጋር በሚያካሂደው ትግል ከግንባር ቀደምነት ደረጃ ላይ የደረሰውን ወዝአደር አብዮታዊ ኃይል ሊያስተባብር የሚችል ኮሙኒስት ፓርቲ በአስቸኳይ እንዲቋቋምና የማጥቃቱ ዘመቻ በበለጠ እንዲፋፋም ማድረግ የሀቀኛ ተራማጆች የጊዜው አጣዳፊና ታሪካዊ ኃላፊነት ነው ። አብዮታውያን ወጣቶችም በስውር ተደራጅተው ሕዝቡን ለአብዮታዊ ትግል በማንቃት በማደራጀትና በማስታጠቅ ላይ በሚገኙት ተራማጅ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል አፍአዊ ሳይሆን ተግባራዊ የትግል ኅብረትና መቀራረብ ተፈጥሮ የወዝአደሩ ፓርቲ እንዲቋቋም በመታገል በኩል ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ። በአንድ የትግል ሜዳ ለአንድ ዓላማ ተሰልፈው በመታገል ላይ በሚገኙ ማርክሲስት ሌኒንስት ወጣቶች መካከል የሚፈጠር የትግል ኅብረት በልዩ ልዩ ተራማጅ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል የሚገኘውን ግንኙነትና ትብብር በይበልጥ ሊያቀራርበው ይችላል ። የእነዚህ ቡድኖች በይበልጥ መቀራረብ ደግሞ ለአብዮታችን ግቡን መምታት ዋና ዋስትና የሆነውንና አብዮታችን በአለበት ደረጃ አመራሩ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነውን የወዝአደር ፓርቲ ለመመሥረት ያስችለናል ። ስለዚህም ሀቀኛ ተራማጆች በወዝአደሩ ግንባር ቀደም መሪነት በመካሄድ ላይ ያለውን የአጥቂነት ዘመቻ ሊያስተባብርና በጠላት ላይ የማያዳግም ድል ለማስገኘት የሚችል ኮሙኒስት ፓርቲ በሐቀኛ ተራማጆች ኅብረትና ውሕደት እንዲመሠረት ቆራጥ ትግል ማካሄድ አለባቸው ። በዚህም ትግላቸው የወዝአደሩን ፓርቲ መቋቋም ለማዘግየት በሚሹ የጠባቡ ቡድን ስሜት ተገዢዎችና ሰርጎ ገብ ከፋፋዮች ላይ ድልን እንደሚቀዳጁና ግንባር ቀደሙን አብዮታዊ ድርጅት እንደሚመሠርቱ ሙሉ ተስፋ አለን ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።